## እንኳን ደስ ያላችሁ

እንኳን ደስ አላችሁ
እንኳን ደስ ያለን
አንበሳው ተሻለው
ፈጣሪ ይመስገን::
ትንሽ አመም አርጎት
ቢሰነባብትም
ስራ ለመጀመር
ዛሬ ነገ አያውቅም::
ትንሽም ቢያስቸግረው
የጤና ጉዳይ
መቼ ድምጹ ጠፋ
ሆኖ አልጋ ላይ::
በርቱ ተዘጋጁ
ሀገር ወዳዶች
አንበሳው ተነሳ
እንኳን ደስ ያላችሁ ያገሬ ልጆች::
ጀግናው ኃይሉ ሻውል
የሕዝባችን ምርጫ
ጉዳዩም አይደለ
አድርባይ ቢንጫጫ
ወደስራ መግባት
ትግሉን ማጠንከር
የእርሱ ዋና ዓላማ
ይቅደም ነው ተግባር::
ግራ የተጋባህ
ተስፋ የቆረጥክ
ጀግናችን ተነስቲል
አያውቅ መንበርከክ
ቆራጥ መሪ አለን
አያውቅ ማወላወል
በተግባር ያሳየ
ለሀገር ለሕዝብ ሲል::
ነቃ ነቃ እንበል
ሀገር ወዳድ ሁሉ
ኢትዮጵያን ለማዳን
ኃይሉን የምትሉ
ሊጀምር ነው ሥራ
እንደለመደው
የተበተነውን ሊያሰባስበው::

ሀገር ወዳድ ከካናዳ
ጥቅምት 27 ቀን 2000